# <u>ኃይለማሪያም ደሳለኝን ተስፋ አታድርጉ</u>

ከአስተዋይ በቀለ

ኃይለማሪያም ወይም ኃይለ ወያኔ ክፍት ወንበር ላይ ቂጢጥ ማለቱ አይገርመንም:: ድሮም አውታንቲ ሾፌር ይሆናል :: ግን መኪናውም መንገዱም ያው ነው :: ምኑ ላይ ነው ዓሥራትነቱ ወይም ተስፋነቱ ? እስቲ እንግዲህ እንዴት እንደሚያፋድስ እናየዋለን::

ዘንድሮ ጉድ እኮ ነው ! የአገር ቤቱ አዘንተኛ ሲገርመን ለካስ በተቃዋሚው ሰፈርም ነጠላ ያዘቀዘቁ ነበሩ :: አገር የማዳኑ ጉዳይ ቀረና እንታረቅ፤ እንቻቻል ሆነ ለቅሶው ፡፡ ኃይለማሪያምን እንደ ኃይለ እየሱስ አርገው ቤዛችን_መድሃኒታችን ነው እያሉም አሸረገዱ :: ገልጃጃው ችኩሉ ምሁር ዓለማየሁ ገ/ማሪያም ደግሞ አዲስ ጠ/ሚኒስትር አዲስ ዓመት በማለት ኃይለማሪያምን ፈገግ በል እያለ ይመክራል :: አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች ይባላል !

ኃይለማሪያም የወያኔ ሸፋን የሆነ መጋረጃ ወያኔ ነው :: ነገር ግን የወያኔን ትዕቢት የሚያንፀባርቅ መልክ የለውም:: ለሚያየው ሰው እንደ መለስ በትዕቢት የሚያስብና የሚሰራ አይመስልም:; ሞኛ ሞኝ ገጽታው፦ጄንጤቆስጤነቱና አናሳነቱ ብዙ ነገሮችን ሸፍነውለት ለሚመለከተው ሰው ሁሉ ነሁላላ መስሎ ይታያል:: እውነተኛው ኃይለማሪያም ግን ከዚህ በስተጀርባ ያለው በመለስ ክሎን የተደረገ ገፅታ ነው ::

እውነተኛው ኃይለማሪያም ከትግራይ ያልበቀለና በሕውሓት የታቀፈ ስንግ ወያኔ ነው :: የልቡ ሀሳብና ምኞቱ ሁሉ ከወያኔ ጋር ልክክ ብሎ አንድ የሆነ ክፉና መሰሪ ነው :: መለስ የመረጠውና ያቀፈው በዚህ ተገዥ ባህሪውና ሰውነቱ ነው ::

በክርስትና እምነቱ ወደ አምላኩ የቀረበና የእግዚአብሔርን ሞገስና ምህረት ያገኘ ሰው እንዳይመስላችሁ ::

የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ጌታን ከተቀበላችሁ በኃላ ተለዩና ለብቻችሁ ሆናችሁ የሥጋን ነገሮች ከድታችሁ በመንፈስ በመመላለስ በጎ ሥራ ሥሩ ነው የሚለው :: ኃይለማሪያም ግን ኃይለ ወያኔ በመሆኑ ጌታን ከተቀበለ በኃላ እንደ ውሻ ወደ ትፋቱ ተመልሶ እንደ አሳማ ጭቃ ላይ እየተንደባለለ ወያኔን ሲያመልክና ሲያገለግል የኖረና ያለ መናፍቅ ነው ::

በድርጊቱ ከወያኔ ፀረ_ ኢትዮጵያ እቶንና ፀረ_ ሕዝብ በደል የፀዳ ፦ከዝርፊያና ከቅሚያ የራቀ፡ በሃሰት የማይምልና የተፀፀተ እንዳይመሳላችሁ :: ለግለሰብ መለስና ለወያኔ የቆመ እንጂ ለአገርና ለሕዝብ ወዳጅም አይደለም::

መለስ በእሱና በተቃዋሚዎች መካካል ተክሎት ያለፈውን ጠላትነትና አገር ያፈረሰ ራዕይ ለመቀጠል ኃይለማሪያም ቃል ስለገባ ሰው ያስፈጃል ተብሎ ነው የሚፈራው ።

ኃይለማሪያም  እንደ አህያ ፈሪ ስለሆነ ከያዘ አይለቅም ነው የሚባለው፡፡ መቆራረጥና መዘልዘል ሳይሆን በጥርሱ መንጨት ነው የሚቀለውና  እንዳይነጭህ በጊዜ ነቅቶ መታገል ብቻ ነው የሚያዋጣው ።

ኃይለማሪያም የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ባለቤት ባለመሆኑ አቀማመጡ ሁሉ ዘራፍ ለማለት ይመስላል እያሉ ሱዳኖችና ግብጾች የቡና መጠጫ አድርገው እየዶለቱበት  ነው ።

ኃይለማሪያም_ዘመም የሆናችሁ ሁሉ ተስፋ ዘርታችሁ ከሆነ ኃላ ሰደድ ሆኖ የሚያጠፋችሁን ገለባ እንዳታፍሱ ከመቁነጥነጥና  ከመቁለጭለጭ መቆጠቡ ይበጃል ።

ከሕዝብ ትግል ጋር ተስፋና የተስፋ ምንጭ አህዱ አምላክ ብቻ ነው ። ከዚህ ውጭ ተስፋና መመኪያ ፈፅሞ የለም።

ኃይለማሪያምን ትተህ
ከሕዝብ ጋር ዘብ ቁም !!

09/25/2012